በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ታህሳስ 21፣ 2012

**የገለልተኛ ብሔራዊ የኢኮኖሚ አማካሪ ምክር ቤት እጩ አባላትን ለመቀበል የወጣ ጥሪ**

መንግሥት የኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራምን በስኬት ለማስፈጸምና ጥራት ያለው የኢኮኖሚ እድገት ለማረጋገጥ የምሁራንና የባለሙያዎችን ምክር እንዲሁም ግብረ መልስ መቀበል ጠቃሚ ነው ብሎ ያምናል። ገለልተኛ ከሆኑ ምሁራንና ባለሙያዎች ሃሳብ መቀበል የፖሊሲን አካታችነት ይጨምራል። የተለያዩ አመለካከቶች ሃገራችን ያለችበትን ውስብስብ የሆነ የድህነትንና የተያያዙ ማኅበራዊ ችግሮችን ለመረዳትና ዘርፈ ብዙ የፖሊሲ አማራጮችን ለመመርመር እና የመፍትሄ ሀሳቦችን ለማመንጨት ያስችላል። እንዲሁም የመንግሥት ፖሊሲዎች በህዝብና በተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በኩል ያላቸውን ተቀባይነትን እንዲጨምር ያግዛል።

**በመሆኑም መንግስት ገለልተኛ ብሔራዊ የኢኮኖሚ አማካሪ ምክር ቤት ለማቋቋም ወስኗል።** ምክር ቤቱ ገለልተኝነቱን ጠብቆ በነጻነት የሚሰራ ሲሆን ከመንግሥት ጋር በየጊዜው ይመክራል።

የምክር ቤቱ አባላት በቁጥር 15 እንደሚሆኑ የሚጠበቅ ሲሆን በሙያቸው የተካኑና የተመሰገኑ፣ በዘርፉ የካበተ የስራ ልምድ ያላቸው፣ ሃገርን የማገልገል መንፈስ ያላቸው ፣ በሥራ ዘርፍ ፣ በጾታና በሌሎች ገጽታዎች ብዝሃነት ያላቸው፣ የሃገራችንን ኢኮኖሚም ሆነ ማኅበረሰባዊ ዕውነታን ጠለቅ ብለው የተረዱ፣ የሃሳብ ልዩነትን በመረጃና በሃሳብ ዉይይት በመፍታት የጋራ መፍትሄ የመሻት ክህሎት ያላቸውእና ከሁሉም በላይ ለሃገራቸውና ለህዝብ ፍቅርና ተቆርቋሪነት እንዲሁም የአገልጋይነት መንፈስ የሚሰማቸው ሊሆኑ ይገባል።

አባላቱን የመለየቱ ሂደት ግልጽና አሣታፊ እንዲሆን መንግስት በይፋ የእጩ አባላትን ጥቆማ ለመቀበል ወስኗል። በመሆኑም ገለልትኛ የብሔራዊ የኢኮኖሚ አማካሪ ምክር ቤት አባል ሆኜ ለማገልገል ፍላጎቱና አቅሙ አለኝ ብላቹ የምታምኑ ኢትዮጵያንና ትውልደ ኢትዮጵያን ምሁራን የግል ማህደራቹን (curriculum vitae) ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባላሉት ተከተታይ 15 ቀናት ውስጥ policyunit@pmo.gov.et የኢሜል አድራሻ እንድትልኩ እንጠይቃለን።

//